EthioLion

# <u>ይሁዳ ሲፈጠር</u>

አሥራደው (ከፈረንሳይ)

አምላክ እያወቀ ይሁዳን ሲፈጥረው ፤
ልጁን እየሱስን ነበር እንዲሸጠው ፤
ባይወለድ እማ ይሁዳ በዚች ምድር ፤
ለክርስቶስ መሞት ማን ምክንያት ነበር ?
ያዳምስ ሃጢያቱ መች ይሰረይ ነበር ?!

በገባለት ቃሉ አዳምን ለማዳን፤
እንዲሸጠው ልጁን ፈጠረ ይሁዳን ፤
ይሁዳን ባይፈጠር ባምላክነት እጁ፤
አብን በቸገረው እንዲሰቀል ልጁ ::
በመስቀል ተሰቅሎ ክርስቶስ እንዲሞት ፤
ይሁዳ እየሱስን መሳም ነበረበት፤
መሳም ያለየለት: ውሉ የጠፋበት፤
ጥላቻና ፍቅር ተደባልቀውበት::
ባይሸጥማ ኖሮ ይሁዳ እየሱስን በጥቂት ጭብጥ ብር፤
እየሱስ: እየሱስ፤ ይሁዳን: ይሁዳ፤ ባላልናቸው ነበር ::

መልካም የፋሲካ በዓል ለሁላችን ::
ሚያዝያ 15/2003 ዓ.ም. (April 23/04/2011)

EthioLion.Com

Ethiopia will prevail!